የቴሌግራም ቻናላችንን ይቀላቀሉ፤
ምርጥ ምርጥ መጽሀፍ በ pdf
እንዲሁም በትረካ ያገኛሉ

@Ethio_Terka

ኢትዮ ትረካ

ደግሞ በቃ እንደዛ ነች ... እየተካሄደ ያለው ነገር ካልጣማቸው ወይም እነርሱ የሚፈልጉት ሳይሆን ሲቀር ንዴታቸው ብልጭ ሲልባቸው ታስተውላለህ። ይህ ቀሪው ማህበረሰብ የሚኖርበትን እውነታ ላለመቀበል የሚያደርጉት ጥረት አካል ነው። የሚፈልጉትን ነገር ሳያገኙ ሲቀሩ ይበሳጫሉ፤ ምክንያቱም ከሀፃንነታቸው ጀምሮ ሲሰራላቸው የነበረ መንገድ ያ ነበርና ነው። ሲነጫነጩና በሕሊናቸው የሚያሳፍር ሃሳብ እያንከላወሱ መሆኑን የሚገልጹ ተግባራትን ሲያከናውኑ ይስተዋላሉ። እነርሱ ግን እንደዚህም ሆነው አላማቸውን እስካሳኩና የሚፈልጉትን እስካገኙ ድረስ አያስጨንቃቸው፤ አያሳስባቸውም።

### ሴቶች የሚፈልጉት ምንድን ነው?

ጥያቄው "እንዲህ ነው" የሚል ቀጥተኛ መልስ ሊቀመጥለት አይችልም። የሥነ-ልቦና ጥናት ዘርፍ አባት በሚል የሚታወቀው ሲግመንድ ፍሩድ እንኳን ስለ ሰዎች ለሰላሳ ዓመታት ከተመራመረ በኋላ መልስ አላገኘሁለትም በሚል ያስቀመጠው ጥያቄ "ሴቶች የሚፈልጉት ምንድን ነው?" የሚለውን ነበር።

እስኪ ጉዳዩን ከሌላ አቅጣጫና በሌላ አቀራረብ እንመልከተው። ሴቶች የተረጋጋ ሰው ይፈልጋሉ (ሁኔታዎችን፣ ራሱን፣ ስሜቶቹን፣ ሌሎች ሰዎችን እንዲሁም እርሷን የሚቆጣጠር ወንድ ትሻለች)። አንተ ሌት ብትሆን ኖሮ ወንዱ የተረጋጋ ስለመሆኑ ማወቅ ብትፈልግ እንዴት ታደርጋለህ "ድንገት ወደ ሌላ ሰው ብሄድብህ በሃይል አስገድደህ ትመልሰኛለህ?" የሚል ጥያቄ ትጠይቀዋለህ? በጭራሽ! ስለዚህ እነርሱም የሚፈትኑን የተረጋጋን መሆን አለመሆናችንን ለመለየት ነው።

"ለሴት ልጅ ቀጥተኛ መልስ አትስጣት - መልስህ አያ የሚል ካልሆነ በስተቀር...የምትፈልገውንም በፈለገችው መልኩ አታሚላላት ወዘተ...የሚባለው በተዘዋዋሪ የምር የፈለገችውን ለመለጠት ነው። ያም የተረጋጋና ራሱን የተቆጣጠረ ወንድ መሆንህ ነው።

ሴቶች ውጥረት ውስጥ መግባት ይወዳሉ። ለምሳሌ የማያቋርጥ ጉትጎታ፣ የፆታዊ ክርክር መፈጠር የመሳሰሉት ይመቿቸዋል። እነዚህ ዘዴዎች ታዲያ ጊዜና ቦታ መርጠህ ካልተጠቀምክባቸው ዋጋ ሊያጡ እንደሚችሉ አስብ። በምትኩ የተለመደና መደበኛ የአጨዋወት ዘይቤን ተከትለህ በየጣልቃው እያስገባህ መጠቀሙ ያዋጣሃል። ሁሉም ነገሮችን ተቆጣጥረህ ቀልድ የተቀላቀለበት ጨዋታህን ማስኬድ ከቻልክ አብራህ ያለችው ልጅ "ዋው! ይሄ ልጅ ቀልደኛ ነው። ግን የምሩን መሆን አለመሆኑ አያስታውቅበትም። ይህን ማወቅ አለብኝ። አይን ያወጣ ተሳላፊም አይደለም። ስለዚህ በተወሰነ ደረጃ ወዶኛል ማለት ነው . . ." የሚል ውስጣዊ ሀሳብ ማብቀሏ አይቀርም።

ቁልፉ ጉዳይ ፈተናን አስቀድሞ ማየት መቻልና ተዘጋጅቶ መጠበቅ ነው። በርካታ ወንዶች ሴቷ መቅበጥ ስታበዛ ነገሩን ሁሉ ብልሽትሽት ያደርጉታል። ቆጣ ስትል "በቃ ተይው አይሆሽ፣ ይቅርታ" ይሏትና ድብልቅልቁን ያወጡታል ወይም ይደናገጣሉ። አንተ ግን ተረጋግተህ መቆየትን መማር አለብህ። አብራህ ያለች ሴት መኮላተት ስትጀምር ከመደነጋገጥ ይልቅ "ምስኪን አሁንም ቱግ ቱግ ማለት አላቆምሽም? እና ምን ይጠበስ? ከሁለት ዓመትሽ ጀምሮ እንደዚሁ ስታደርጊ አድገሽ ምንም ለውጥ አላመጣሽም" በላት።

ሌላው ልብ ልትል የሚገባህ ጉዳይ ደግሞ ሴቶች ያልፈለጋቸው በሚመስላቸው ወንድ ያለ ቅጥ መሳባቸውን ነው። በቃ ሴቶች እንደዚያ ናቸው፡- እንደ ጥላ አይነት። ስትከተላቸው ይሸሹሃል ስትሸሻቸው ደግሞ ይከተሉሃል። ምን አይነት ስሜት እንደሚሰማቸው ታውቃለህ? "ኦ! ይህ ልጅ ቀልደኛ ይመስላል። ታዲያ እኔንም ከሌሎች አስጠሊታ ሴቶች መድቦ አብሮኝ መተኛት አልፈለገም ብዬ ለማመን አልችልም። ነቁ ነኝ የሚል አይነት ይመስላል። ልማርከው ከቻልኩ ይገርመኛል። ከማረክሁት በኋላ ግን እርሱን አያድርገኝ እንደሌሎቹ አልጫ ወንዶች እወረውረዋለሁ..." የሚል ነው። ስለዚህ አንዴ እንደዚህ አይነት ጨዋታ ከጀመርክ እስከ መጨረሻው መጽናት አለብህ - እስክ መጨረሻው መጨረሻ። ገባህ?

አሁንም እንደገና ሴትን በደንብ ስለማስተናገድ ጉዳይ እናንሳ። እስኪ ከዚህ ጋር በተያያዘ የአንድ ወዳጃችንን ልምድ እንመልከት፡- እሱ ሴት በደንብ ነው የሚንከባከበው። ሁሉም "እንደ አንተ የሚንከባከበኝ ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም" ይሉታል። እርሱ ለራሱ አሿፊና ፌዘኛ ሆኖ ሳለ እንዴት ይህ እውነት ሊሆን ይችላል?

መልካም በጣም ቀላል ነው . . . በራሱ ጊዜ ጥሩ ጥሩ ነገሮችን ያደርግላቸዋል። በድንገት ካርድ በመግዛት ወይም ጣፋጭ በሆነ ደብዳቤ/ ኢሜል ያስደንቃቸዋል፤ ማሳጅ ያደርጋቸዋል። እዚህ ላይ ስንመለከት ሴቶችን የሚገዛቸው የልጅ ነገሮችን በቁጥጥር ስር ማድረግ መቻል ነው።

በሚቀጥለው ጊዜ ለምታገኛት ሴት ምን መልበስ እንዳለባት ንገራት . . . ምግብ ምረጥላት እና እንድታምንህ ንገራት። "ላመኝ" ካለች እምቢ በላት ግን ቆይተህ አንተ ስትፈልግ ሳማት . . . የምትወደውን ቸኮላት

ከጠየቀችህ አትስጣት . . . ሌላ ጊዜ ስታገኛት በድንገት ሰጥተህ አስፈንድቃት። ገባህ?

ለማጠቃለል ያህል እንደ ዋና መሳሪያ አድርገህ የምትጠቀምባቸው መመሪያዎች እኚውልህ፡-

1. ለሴት ልጅ ፈጽሞ ቀጥተኛ የሆነ መልስ አትስጥ፤ መልስህ አይሆንም የሚል ካልሆነ በስተቀር። "እዚህ ጋ እንቀመጥ?" ብትልህ "አይ ቀጥሎ ያለው ቦታ ይሻለናል" በላት። "ቀሚሴን እንዴት አየኸው?" ብትልህ "በሂደት የምወደው ይመስለኛል። ግን ውሳኔ ከመስጠቴ በፊት ትንሽ ስትሞናደይበት ማየት እፈልጋለሁ" በላት። "ነገ ደውልልኝ" ብትልህ "አይ ነገ አንቺ ልትደውይልኝ ትቺያለሽ። ትፈልጊኝ የለ እንዴ?" በላት። የፈለገችውን ነገር ፈጽሞ በቀጥታ አትስጣት። "ቤት ና" ብትልህ "አሁን ሥራ በዝቶብኛል። በኋላ እመጣለሁ" በላት። "በጣም አስፈልገኸኛል ፍቅር እንስራ" ብትልህ "ጥሩ ሃሳብ ነው። ግን ትንሽ መጠበቅ ይኖርብሻል ደግሞ እኮ ገና ስሜሽ አልጨረስኩም" ነው የምትላት . . . ግልጽ ነው? የፈለገችውን በቀጥታ አትስጣት። በጭራሽ!
2. ስለተናገርከው ወይም ስላደረግኸው ነገር ቅሬታዋን ብትገልጽ በድርጊቱ ግፋበት። "እንደዚያ ስትል የምር አልወድም" ብትልህ "እረ ባክሽ! ከፈለግሽ መውጣት ትቺያለሽ። ምክንያቱም ደጋግሜ ልለው እየተዘጋጀሁ ነው" በላት።
3. ሴቶች ከእነርሱ ጋር አብረህ የምትሄድ መሆን አለመሆንህን ለማወቅ በተደጋጋሚ ይፈትኑሃል። ልክ ፈተናቸው ሲያበቃ ያገቡሃል ወይም ጥለው ይሄዳሉ።

እንተ ጉዲይህ ከቆንጆ ሴት ጋር ከሆነ ብዙ ትርጉም የማይሰጡ ነገሮች ሲታደርግ ታያታለህ። ግን ደግሞ በእርሷ ቦታ ሆነህ ብታየው ትርጉም የሚሰጥ መሆኑን ታውቃለህ። ቆንጆ ሴቶች የፈለጉትን ነገር ሁሉ በቀላሉ ማግኘት ይችላሉ። እነርሱ አጥብቀው የሚሹት ፣ የሚፈታተናቸውን ወንድ ማግኘት ነው። ብዙ ወንዶች ከሌሎች ወንዶች ምንም የተለየ ነገር ሳይሰሩ ቆንጆዋን ሴት በእቅፋቸው ማስገባት የሚችሉ ይመስላቸዋል። ይህ ፍፁም ሞኝነት ነው።

4. የተደበላለቀ ስሜት ፍጠርባት። ንጹህ ጓደኛዋ መሆን እንደምትፈልግ ንገራትና ላማት። የለራችው ስራ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ንገራትና ላማት። አሪፍ ነገር ስትሰራ መቀመጫዋን ቸብ አድርጋት። ለአንድ ነገር ሁለት የተለያዩ ምላሾች ስጣት። ለምሳሌ መጥታ ጉልበትህ ላይ ቁጭ ስትል በመጀመሪያው ጊዜ ላማት በሁለተኛው ደግሞ ገፍተህ አስነሳት። የሚቀጥለውን አታስተንብይ - በጭራሽ።

እስካሁን ሁልጊዜና በጭራሽ ስንል መቶ በመቶ ሳይሆን በተቻለ መጠን ማለታችን ነው። ቁም ነገሩ "እየሳቀች ነው? ተመችቷታል? ደስ ብሏታል?" የሚለው ነው። ያኔ ከላይ ያልናቸውን ነገሮች ገታ ማድረግ እንዳለብህ ትረዳለህ።

### *ዐይነ-ግቡ ሴቶች አደባቸው ብዙ ነው*

እዚህ መጽሐፍ ውስጥ ቀደም ብሎ ተነስቶ ስነበረ አንድ ነገር እናስታውስህ። "ወንዶች ቆንጆ ሴቶችን ነጋ ጠባ ይከታተሏቸዋል።" "ተፈላጊ" ሴቶች ሐብታም፣ ቆንጆም ይሁኑ ዝነኛ ብቻ ምንም ቢሆኑ እንደ

ንግስት መታየትን ለምደዋል። ይህ ደግሞ የእነርሱ ስህተት አይደለም። ቆንጆ ወንዶች እንኳን ሲንጠባረሩ በማህበረሰቡ ዘንድ እንደጥሩ ይታይላቸዋል። ይህ ሰው የመሆን አንዱ ክፍል ነው። ነገሮች ሁሉ ቢሟሉልን ሁላችንም እንደዚህ ልንበላሽ የምንችልበት አጋጣሚ አለ።

ተሞላቀው ከማደጋቸው የተነሳ እነዚህ ቆንጆ ሴቶች ቅብጠት ያበዛሉ። በእርግጥ በየደረሱበት ጠብ እርግፍ የሚሉሏቸው ወንዶች አስተዋፅኦም አለበት። ነጋ ጠባ ስለሚጀነጀኑና እንዳሻቸው የሚሽከረከሩላቸው ወንዶች በየቦታው ስላሉ አንተ ድንገት ብቅ ብለህ ለዛ ያለው ጨዋታ ስትጫወትና የተለመደውን የውሸት ጨዋታቸውን ችላ ስትልባቸው (ስታስቅባቸው፣ እንደሚፈልጉህ ስትነግራቸው፣ ስታሾፍባቸው፣ ስለስራ ቤት ደመወዝ ወዘተ ሲጠይቁህ መልስ ስትነሳቸው እንዲያውም ትንሽ አሰብ አድርገህ "እዚህ ቤት እንደሚሰባሰቡት ተራ ሴቶች አንቺም የጥያቄው ዝርዝር ደረሰሽ?" ብትላት) "ዋው! ይህ ሰው የምር ልዩ ነው" ብላ እንድታስብ ታደርጋለህ። ራስህን ማካበድህ ከቀልዱ ጋር ተዳምሮ ትኩረቷን ይስበዋል። ጨዋታው የተለመደውን አስተሳሰብ በልዩና በሚስብ ባህሪ ማቋረጥ ነው።

ቆንጆ ሴቶችን የሆነ ዘዴ ተጠቅመህ ከነበሩበት ማቋረጥና ትኩረታቸውን ማግኘት ይኖርብሃል። ከዚያ ስሜት ሊገዛ የሚችል ጨዋታ ፈጥረህ ሀሊናዋ የሚሻውን አካሄድ መቀጠል ትችላለህ።

አዲስ ያገኘሃትን ሴት በጨዋታ እያስመሰልክ ተርባት። ያኔ የምታስበው "ይሄ ሰው ዱርዬ ነው። እኔ አያገባኝም" ወይም "በጣም ቀልደኛ ልጅ ነው። እንዲያውም የምፈልገው ዐይነት ይመስለኛል" የሚል ይሆናል። ሴት ልጅን በጣም እንዳያስከፋት አድርገህ ደካማ ጎኗን እያነሳህ

ስትተርባት በእንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ እንደመጣል ይቆጠራል። ፈዝዘ ውሽት ነው ብላ ልትክድ አትችልም ምክንያቱም እየሳቀች ነዋ! የምሯን ልትጠላህ አይቻላትም ምክንያቱም ተልድ ነዋ! እስቲ ይህንን የበለጠ ለማብራራት እንዲመች አንድ በመላው አሜሪካ ስሙ የገነነ የጠበሳ አማካሪን ልምድ በራሱ አገላለጽ እንመልከት።

"ነገሮችን ለማድረግ ሴቶችን ፈቃድ አልጠይቅም። የነገራቸውን አካሄድ አስተውልና ምላሽ የሚሆነኝን መላ እቀምራለሁ። ከዚያ የምፈልገውን እርምጃ እወስዳለሁ። ምልክቶቿን አነብና መቼ እንደምፈታተናት እጠባበቃለሁ። ከሌት ልጅ ስልክ መቀበል እንዴት እንደምችል ረዥም ጊዜ ወስጄ አጠናሁ። ይህ ግን ለብቻው ስኬት ማለት እንዳልሆነ ተረዳሁ። ከዛ ሴቶች ወደ ቤቴ እንዲመጡ ማድረግ እንዴት እንደምችል ተማርሁ። ግን ይኸም ሙሉ ስሜት ሊሆን እንደማይችል ገባኝ። በስተመጨረሻ የገባኝ ነገር ከሌት ልጅ ጋር ስሆን ሙሉ ጊዜውን እኔ መምራት እንዳለብኝ ነው። ትልቁ መርሔ ደግሞ "እርሷ እንግዳዬ ነች ማስተናገድ ያለብኝ እኔ ነኝ" የሚለውን ነው። "ይቅርታህን አታጨናንቀኝ ለምን ትረብሻለህ፣ በቃ ተወኝ" አይነት ጨዋታ ስትጀምረኝ ከት ብዬ እስቅባታለሁ። ልክ እንደዚያ ሳደርግ ምን እየተካሄደ እንደሆነ ግራ ይገባታል። ከዚያ "ለምን ትቀልጃለሽ...ለምን በአገር ሰላም ታጨናንቂኛለሽ?" እላታለሁ። ያኔ የተለመደው አይነት ጨዋታዋ አጠገቤ አለመድረሱን ትረዳለች። ወጥመዷ አለመስራቱም ይገባታል። በፍፁም አልበሳጭላትም ወይም በስሜታዊነት አልናገርም። እንደዚህ ስሆን ካየች ይህ ለእርሷ መልካም አጋጣሚ ይሆንላታል። ደጋግማ ትጠቀምበታለች።

እኔ አዲስ ሴት ሳገኝ ገና ከጅምሩ ለረዥም ጊዜ ግንኙነት ትሆነኛለች በሚል ፈርጄ አላውቅም። ከወደድኳትና ደጋግመን ስንገናኝ ከተመቸችኝ እንደ አንድ አማራጭ እወስደዋለሁ። በኔ ግምት ልክ በጣም አሪፍና ቆንጆ ሴት ለወንዶች ብርቅ እንደምትሆን ሁሉ ጠንካራ፣ አስደሳችና ስሜቱንና ሁኔታዎችን የሚቆጣጠር ወንድ ለሴቶች ብርቅ ነው። ወዴት እያመራሁ እንደሆነ አያችሁ?

ሴቶችን በፍቅር የሚማርኩ በርካታ ወንዶች አውቃለሁ። ያወቅኋቸው ልምድ እንዲያካፍሉኝ በመፈለግ ሂደት ውስጥ ነው። ብዙ ሴቶች እነዚህን አይነት ወንዶች ለማግኘት የታደሉ አይደሉም። ሲያገኙዋቸውም ቀበጥና አስጠሊታ ሴት ሆነው ስለሚቀርቡ ሁኔታዎችን ያበላሿቸዋል። ወንዶቹ ሲተዋቸው በጊዜው የደረሰላቸውን አጋጣሚ ይጠቀሙና ይረጋጋሉ።

ሴላ ዘግይቼ የተረዳሁት አንድ ነጥብ አለ። በአብዛኛው ከአስር ዓመት በላይ ወንተው የቆዩ ትዳሮች አንድ የሚጋሩት እውነት አለ። እርሱም በትንሹም ቢሆን ባሏን የምትቆጣጠረው ሴቷ መሆኑን ነው። ስለፍቅር የሚያትቱ ብዙ ድርሰቶችን ተመልከት። አንዲት ሴት አስቸጋሪ ወንድ ታገኛለች። ታላምደዋለች። ከዚያ ጥሩ ስነ-ምግባር እንዲያዳብር ታደርገውና ተጋብተው በደስታ ይኖራሉ።

እዚህ ላይ ወደዋናው ጉዳይ እየመጣሁ ነውና ተከታተለኝ።

እኔ ከአንዲት ልጅ ጋር እየተነጋገርኩ እያለ አንተ የሆነ ቦታ በአቅራቢያችን ሆነህ ብትሰማኝ ልትለኝ የምትችለውን ሳስበው "ይሄ ልጅ የመጨረሻ ቀልደኛ ነው። ግን ያበዛዋል። ማለቴ በትምክህት የተሞላ ነገር ሊናገር ትንሽ ነው የቀረው። ግን እንዴ እርሱ እንደዚያ ባለ ቁጥር ልጅቱ

የበለጠ እየተሳበች መጣች እኮ ... ይገርማል!" የምትል ይመስለኛል እንጅ "ይሄ ሴቶች የሚጠሉት ዓይነት አተራማሽ ነው" አትልም። ይህን ያልሁት ከላይ የምተገብራቸው ዘዴዎች ሁሉ የሚፈለገው ዓይነት ባህርይ አካላት መሆናቸውን እንድትረዳ ነው።

ፈዘኛ ሆነህ መዝለቅ ስትችል ሴቶች በጣም ይደሰታሉ። ለእነርሱ ላትጫወት የቀረህ ሲመስላቸው ተስፋ ይቆርጣሉ። መጨረሻ ላይ ልባቸው ቀልጦ እንደሚወዱህ ያሳዩሃል። በእንደዚህ አይነቱ አቀራረቤ አፍ አውጥታ የጠየቀችኝ ልጅ አስታውሳለሁ። በነገራችን ላይ ልጅቱ የምትጠራኝ ጉረኛ፣ ትምክህተኛ፣ ደረቅ ... እያለች ነበር። ግን እንደዚያ ስትል ትስቃለች (ቁልፉ ደግሞ እርሱ ነው)። ፈዝ ከመጠነኛ ትምክህት ጋር ቀላቅሎ እንደመጠቀም ውጤታማ ነገር የለም። እንደ አየሩ ፀባይና እንደሁኔታዎች ራሴን እቀያይራለሁ። ቀልብ የሚስቡ ነገሮችን ለሴቶች በራሴ ጊዜ አደርግላቸዋለሁ። ወደ ግብረ ስጋ ግንኙነት ስንመጣ ሴቶች የሚወዷቸውን ነገሮች አጠናለሁ፣ እማራለሁ። አላማዬም እስካሁን ካጋጠሟት ወንዶች ሁሉ የተሻለ አርኪ መሆን ነው።

እነዚህን ነገሮች ሁሉ በአግባቡ ማጣመር ከቻልክ የፈለግሃት ሴት በአንተነትህ አፍቅራህ እንድትዘልቅ ለማድረግ መንገዱን የምትመራበት ችሎታ ይኖርሃል። አስታውስ ሴቶች ቀጥተኛ አይደሉም። ትርጉም ያለው ነገር ስታደርግላቸው ትርጉም የሌለው ነገር ያደርጉብሃል። ትርጉም የሌለው ነገር ስታደርግላቸው ደግሞ ትርጉም ያለው ነገር ያደርጉልሃል። ብልጠቱ የትኞቹን ትርጉም የሌላቸው ነገሮች መስራት እንደሚገባ ለይቶ ማወቅ ነው።

## ሴቶች የሚፈልጉት ምን ዓይነት ወንድ ነው

በወንድና ሴት ልዩነትና አንድት ላይ ብዙ የሚያከራክሩ ነጥቦች አሉ። በእኔ አመለካከት ወንዶችና ሴቶች ይለያያሉ። ለተመሳሳይ ጥያቄዎች የተለያዩ መልሶች ሊሰጡም ይደመጣሉ። በእኔ እምነት ሴቶች ወንዳወንድ ለሆኑ ወንዶች የሴትነት ምላሻቸው ጠንካራ ይሆናል። በራሴ በጣም የምተማመን፣ በመጠኑ ትምክህተኛና የበላይ ሆኜ ስገኝ ሴቶች ይበልጥ ስሜታዊና ወሲባዊ ምላሽ ይሰጡኛል። (እዚህ ላይ እያወራሁ ያለሁት ሴት ልጅን እንደ አሀያ ስለመነረት ወይም ስሜቷን ስለመጉዳት አይደለም)። ብዙ ሴቶችን በጉዳዩ ዙሪያ አናግሪያለሁ። ለፈስፋሳ ወንድ በሴቶች ዘንድ እንደማይፈለግ ነው የተረዳሁት። ሴት ልጅ የተለያዩ ነገሮች አስፈለጉኝ ልትልህ ትችላለች። "ወይን አማረኝ" ትልሃለች ወይም እንዳመማት ዓይነት ልትሆን ትችላለች። ሁሉም ግን ከጀርባቸው የሆነ ፈተና አለባቸው። ደካማ አይናፋርና ታዛዥ ከሆንክ እርሱን እርግፍ አድርገህ ተወው። ልፍስፍስና አሽቃባጭ ወንድ መሆን የለብህም። እኔ ሴት ልጅን "አይሆንም" ስላት በእርጋታ ነው። ልፍስፍስ ወንዶች ግን ቁጣ በተቀላቀለበት ድምፅ "በፍፁም" ይላሉ። ገባህ?

### *ሴቶችን መፎገር*

አንድ ጊዜ የሆነች ልጅ አገኘሁና ወደ መኪና ውስጥ ስንገባ እጇን ያዝኩት ... ከዛ ለቀቅሁትና "ገና ከአሁኑ እጅ መያያዝ አይቻልም" አልኳት። ልክ እርሷ ያመነጨችው ሃሳብ እንደሆነ። ከዛ ምላ ላይ እጇን እንድትይዘው ሰጠኋት። ልትይዘኝ ስትል ሳትነካኝ ሰበሰብኩት ... ካዛ በድጋሚ ደገምኩ "ከምር አይቻልም" እያልኳት። በመጨረሻ ላይ ከምላ በኋላ እጇን ወደ እጇ ሳስጠጋው ለመያዝ አልፈቀደችም። ምክንያቱም

በጭንቅላቷ እንደማይቻል ደምድማለች። ከዚያ እኔው እጇን ያዝኩትና መልዕክት እንዲያስተላልፍ አድርጌ አሻሽሁት። በኋላ ላይ ሳቅፋት ቀድማ ጉንጨንና አንገቱን ሳመችኝ። ለዚህ ድርጊቷ ደግሞ በጣም ወቀስኳት። ገባችሁ ጨዋታው? እኔ የድራማውን የመጀመሪያ ክፍል እጫወተውና እርሷ ያንኑ ለመስራት ስትሞክር ጥፋተኛ አድርጌ እከሳታለሁ። እንደዚህ ዐይነቱ ጨዋታ ለብዙ ወንዶች ትርጉም አይሰጥም፤ ለሴቶች ግን እንደተዐምር ነው።

አንዳንድ ሴቶች ደግሞ ገና ከጅምሩ አፍረጥርጠህ እንደምታውቃቸው ስትነግራቸው፣ ስልካቸውን ተቀብለህ ነገረ ስራቸው የደስ ደስ ያለው መሆኑን እያነሳህ ስትስቅባቸው ቀጥለው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ግራ ይገባቸዋል። ጨዋታውን አንተ እንዳሻህ እንድትመራው ይተውሃል። ሴቶች እንደዚህ ዓይነቱን ነገር ይወዱታል። ምክንያቱ ደግሞ እንዲህ አይነት ወንድ ለማግኘት ስለሚቸገሩ ነው። እናም እነዚህን ወንዶች በሚስጥር ይወዷቸዋል። ይህንን ሁሉ ዝርዝር መረጃ የምግራችሁ ሰምታችሁ ሄዳችሁ እንደለመዳችሁት እንድትሽቆጠቆጡ ሳይሆን ራሳችሁን እንድትቀይሩበት ነው።

ሌላኛው መንገዴ ደግሞ ገና ከመጀመሪያው ንፁህ ጓደኛ ልትሆነኝ እንደምትችል እነግራታለሁ። ከዚያ በውስጤ መሳቅ እጀምራለሁ። ምክንያቱም እንደዚያ ማለቴ የሚያጭርባት ነገር አለ። "እንዴ ይኼ ሰው ከእኔ ይበልጣል። ወጥመዶቼን ሁሉ ፉርሽ ሊያደርግ የተነሳ ይመስላል። ቆይ ግን ምን ቢጎድለኝ ነው ገና ከጅምሩ ስለ ጥሩ ጓደኝነት የሚያወራው። አልወደደኝም ማለት ነው?" ቁልፉ ነጥብ እየገባህ ነው? ሁሌም እንድትስብ፣

እንድትወዛገብ አድርጋት። በፍፁም ሰፍ አትበል። ያለበለዚያ እዚያው የድሮ ጨዋታዋ ውስጥ ተመልሳ ትገባለች።

ሌላው ደስ የሚለው ነገር ሌቶች ከቀጥተኛ ቋንቋ ይልቅ የሚገባቸው የምልክት መግባቢያ ነው። ህፃናት ወንዶች በህፃናት ሌቶች ማሾፍ የሚጀምሩት ገና በ8 ዓመት ዕድሜአቸው ነው። ሌት ህፃናት ይወዱታል። ይህንኑ ጨዋታ በ18፣ በ28፣ በ38፣ በ48 ዓመት ዕድሜአቸውም ይፈልጉታል። ይመቻቸዋል። የምሬን ይሁን አይሁን በማያስታውቅ መልኩ ደካማ ጎን ፈልጌ እስቅባቸዋለሁ። ይወዱታል። ሌቶቹ በምልክት መቀበልም ሆነ ፍንጭ መስጠት እጅግ ያስደስታቸዋል። ሌት ልጅን "እወድሻለሁ" ከምትላት "አንቺ እኮ ትወጂኛለሽ" ብትላት የበለጠ ደስ ይላታል። መልዕክትህንም ታስተላልፋለህ። ተረዳኸኝ?

አሽሙራዊ አገላለፅን አዘውትሬ እጠቀማለሁ እንጂ ፊት ለፊት የምፈልገውን ተናግሬ አላውቅም። እስኪ አንድ ምሳሌ ልንገርህ።

ከሌት ልጅ ጋር ወሲብ መፈጸም ቢያምርህ እንዲህ ልትላት ትችላለህ "ዛሬ ለምን ወሲብ አንፈፅምም?" እስቲ ሞክረውና ውጤቱ ምን ያህል አጥጋቢ እንደሆነ መዝግብ። በሌላ መልኩ እንደሚከተለው ልትሞክረው ትችላለህ። እየተጨዋወታችሁ ባለበት ሰዓት ድንገት ተነስተህ ቁም። እጇን ያዝና አስነሳት። ከዚያም እቀፋት። ከዛ ተመልሰህ ቁጭ በል። ተመልሳ ቁጭ ካለች በኋላ "ማቀፍ ስለፈለግሁ ብቻ ነው" በላት። ከዚያ ትንሽ ቆይተህ እቀፋት። ስታቅፋት አንገቷን እያሻሸህ እንዴት ጥሩ ጥሩ እንደምትሸት እየነገርካት ይሁን። እንዳታቆመው። ደጋግመህ በዚህ መንገድ እቀፋት። ከደቂቃዎች በኋላ እየጋለች መምጣቷን ትነግርሃለች። አየህ! ሁለት የተለያዩ መንገዶች ግን ደግሞ ወደ አንድ ውጤት የሚያደርሱ

ልዩነታቸው ሁለታቸው ከመጀመሪያው በመቶ እጥፍ የተሻለ ውጤታማ ያደርግሃል።

ወንዶች ቦታና ጊዜውን ወስነን ከሴት ልጅ ጋር መተኛት እንፈልጋለን። ሴቶች ግን በታሰበና በታቀደ ሂደት ውስጥ ሳይሆን አጋጣሚ በሚመስል ሁኔታ ከወንድ ጋር መተኛትን ይመርጣሉ። በተለይ ደግሞ በህብረተሰቡ ውስጥ "ነውር" ተብለው የተፈረጁ ነገሮችን በድንገት ሲያልፉባቸው ደስ ይላቸዋል። ለምሳሌ በድንገት ቤትህ በመጣችበት ወቅት እጇን ማሻሸት ጀምረህ ብትስማት ... ወዘተ ሳይታሰብ የተደረገ አድርጋ ስለምትወስደው በቀላሉ ትሸነፍልሃለች። ስለዚህ ከሴት ልጅ ጋር የሚኖርህን ስኬት ለማብዛት እንደዚህ ዓይነት አጋጣሚዎችን በብዛት ፍጠር። ሴቶች ሳያስቡት ሁኔታዎች ውስጥ ገብተው መገኘት እንጅ እየተጠቀምክባቸው እንደሆነ ዓይነት በማሰብ መጨናነቅ አይፈልጉም።

ሌላው ደግሞ የሴቶችን የሰውነትና የፊት እንቅስቃሴዎቻቸውን ቋንቋ እንደማውቅባቸው የምገልፅበት አንድ መንገድ አለኝ። አንድ እንቅስቃሴ ስታሳይ በመተርጎም የሆነ ነገር ማለት እንደፈለገች በማስመሰል አስቀድሞ መልስ መስጠት ነው። ለምሳሌ አንዲት ሴት እጇን ጎተት አድርጋ ብትይዘው "ከምርሽ ነው?" እላታለሁ። ልክ እርሷ የፈለገችኝ አይነት በማስመሰል። ሴቶች የሚፈልጉትን ነገር በሰውነትና በፊት እንቅስቃሴ በመግለፅ በጣም የተካኑ ናቸው። ይህንን አንተም ልብ ሳትል አልቀረህም። በቃላት የሚገልፁት ማንነታቸው ውሱን ነው።

ስሜታቸውን በምልክት እንዴት እንደሚገልፁ አንዴ ቁልፉን ካገኘኸውና ቀልድ እየቀላቀልክበት ማወቅህን ካሳወቅሃቸው ይሸልሙሃል። (ይህን አወቅሁ ብለህ ደግሞ ጊዜህን ሁሉ እንደ ሴቶች በምልክት

በማውራት ወደ ቀድሞው ሴታሴትነትህ እንዳትመለስ። መጥነህ ነው መጠቀም ያለብህ። ማወቅህን ለማሳወቅ እንጂ መሰረታዊው የአቀራረብ ዘዴህ ሊሆን የሚገባው እሱ አይደለም። ይህንኑ ስህተት ወንዶች በተደጋጋሚ ይሰሩታል። እድሜያቸውን ሴቶችን በመኮረጅ የሚጨርሱም አሉ። እንደዚያ አይደለም ማድረግ ያለብህ አንተ)

አስቲ ሴት ልጅ መቅረብን በምናቤ እንዴት እንደማየው ልንገርህ። ቀልደኛና ተጫዋች ነኝ። መስመሯን አስታታለሁ። አሾፍባታለሁ። ፋታ እንኳን አልሰጣትም። በእኔ እምነት መልክህ ምንም ይምሰል ምን፣ ቁመትህ ይጠርም ይርዘም፣ ዕድሜህም ያሻውን ይሁን ለሴት ልጅ ቁምነገሩ ቀልደኛነትህ ነው። ቁመትህ 1.40ሜ ቢሆን ወይም አንድ አይን ባይኖርህ እርሱ አይደለም የፍቅር ቁልፉ - በሴቶች ዘንድ። በተከታታይ ልታስቃቸው ከቻልክና ጥሩ ስሜት በውስጣቸው እንዲንሸራሸር ማድረግ ከቻልክ ያፈቅሩሃል። የዛሬ ሦስት ዓመት አካባቢ የማሳቅን ጥበብ ለማጥናት ወሰንኩኝ። ምክንያቱም እዚህ ዓለም ላይ ከሚያስቅ ነገር በተሻለ ሰዎች ምላሽ የሚሰጡት ነገር እንደሌለ ስለገባኝ ነው። ወደ ስድስት የሚጠጉ የቀልድ መጽሐፍትን ገዝቼ አነበብኩ። ከመካከላቸው አንዱ በጣም ጥሩ ነገር አስተማረኝ። ቀልደኛ የመሆን ብዙው ክፍል አቀላለዱ እንጂ ቀልዱ አይደለም። ሴቶች ቀልድ አብዝተው እንደሚወዱ የገባቸው በርካታ ወንዶች ቀልዶችን ለማጥናት ይወጣሉ፣ ይወርዳሉ። የሚያስቀው ነገር በርካታ ቀልዶችን ተምረው መጥተውም ሴቶቹ ሳይስቁላቸው ይቀራሉ። ለምን ቢባል ሴቶቹ ቀልባቸው ከቀልዶቹ ሳይሆን ከአቀላለዱ በመሆኑ ነው።

ዛሬ ዛሬ ሴቶች ይደውሉልኛል። እኔ ጋር መሆን እንደሚፈልጉ ይነግሩኛል። ይህ ምናልባት ለአንተ የሚገርምና "ወይ ጉድ" የሚያሰኝ ነገር

ሊሆንብህ ይችላል። ነገር ግን አንተም እኔ የምጠቀምባቸውን ክህሎቶች ከተጠቀምክ እርግጠኛ ነኝ በቀላሉ እዚህ ደረጃ ላይ መድረስ ትችላለህ። ስለዚህ ሴቶች የሚፈልጉት ተፈጥሮ ምን ዓይነት ነው የሚለውን ልንገርህ።

በአንድ ቀን ትውውቅ ብቻ ሴቶችን እንደፈለገው የሚያደርግ አንድ ዓደኛ አለኝ። ስልክ ቁጥር መቀበልና ቀጠሮ ማስያዝ ለእርሱ ቀላል ነው። እርሱ ልክ እንደማሽን ነው። እንደሚለው ከሆነ ቀልደኛና ምፀተኛ ሆኖ ነው የሚቀርባቸው። "መንቀባረርና ራስን ማካበድ ብቻውን የሴቶችን ስሜት ያቀዘቅዘዋል" ይላል። ቀብራራነትንና ቀልድን አዋህዶ መጠቀም ግን ሴቶችን እንደ ማግኔት በማይታመን ፍጥነት ይስብልሃል።

እኔ በሂደት አዳብሬዋለሁ የምለውን ስብዕና እንደሚከተለው አጠቃልዬ ልግለፀው።

"እንዲት ልጅ ልታጠምደኝ እንደሆነ አስቀድሜ አውቃለሁ። በቀላሉ እንደማትይዘኝ ለማላወቅ እስቅባታለሁ፤ ግዴለሽ እሆንባታለሁ። በቃ በተቻለኝ መጠን በጥያቄ እንድትወጣጠር አደርጋለሁ። አሽሙረኛና የሚያደነጋግጣት ወንድ እንደምትወድ ስለማውቅ እንደዚያ አደርጋለሁ። ውጭ ወጪኔን የመውደድ ምልክት ብታሳየኝ እንኳን እስከምታረጋግጥልኝ ድረስ ማደነጋገጥና ማፌዜን እቀጥላለሁ። እዚህ ደረጃ ላይ ስንደርስ ደግሞ ከፈለግሁ ልተዋት እንኳን እችላለሁ።"

ግራ የሚያጋቡ ነገሮችን ማድረግ እወዳለሁ። ለምሳሌ ቡና ቤት ውስጥ አጠገቤ አንዲት ሴት ካለች ዞር እልና ኮስተር ባለ ድምፅ "በፈጠረሽ ቡና ቤት ውስጥ በዚህ ሰዓት ምን ትሰሪያለሽ? የተረጋጋ ወንድ አጣሽ? ወይስ ተስፋ ቆርጠሻል?" እላታለሁ በተቋጠረ ፊት ወይም "እባክሽን ላትነካኪኝ ትችያለሽ?" እላትና አይን አይኗን አየዋለሁ። ያኔ የተናገርኩት

የምፈን ይመስላታል። ግን ደግሞ በትንሹ የምትጠራጠርበት ክፍተት አተውላታለሁ። እኔ እንደምፈልገው ደንገጥ ብላ "ውይ ይቅርታ የነካሁህ ስላልመሰለኝ ነው" ካለች ቀጠል አደርግና "መንካት እንኳን ነክተሽኛል። ከአሁን በኋላ ግን የምትነኪኝ ከሆነ በደንብ ብትነካኪኝ ይመቸኛል" ስላት ትስቃለች። አንዳንዴ ደግሞ እየቀለድኩ እንደሆነ ገብቷት "ኧረ! በጣም ነካሁህ እንዴ!" የምትለኝ ከሆነ ፊቱ ኮስተር እንዳለ "እዎ መነካት አልወድም። ትንሽ ራት ብለሽ ብትተመጭ ደስ ይለኛል" እላታለሁ። አልፎ አልፎ ደግሞ ቀዝቃዛ ሴቶች ያጋጥመኝና ምንም እንዳልተፈጠረ ፊቴን አዙሬ እሄዳለሁ። በእንዲህ ዓይነቱ ጨዋታ ላይ መገንዘብ ያለብህ በጨዋታው አስከመጨረሻው መዝለት እንዳለብህ ነው። ያለበለዚያ ግን ገና የወደደችህ መስሎ ሲሰማህ ወደ ቀድሞ ሴታ ሴትነትህ ከተመለስክ ተጫውታብህ ትሄዳለች። "በተላሉ አልገኝም" የሚለውን ተፈጥሮህን አስከመጨረሻው ጠብቀው።

## *ቀልደኛ ለመሆን አጭር ስልጠና*

እዚህ ላይ ቀልደኛ መሆን ትችል ዘንድ ያዘጋጀሁልህ አጭር ስልጠና አለና በአትኩሮት ተከታተል።

ጥሩ ያስቃሉ የሚባሉ መጽሐፍትን ግዛና አንብብ። ከዚያም ከሪስ ሮክ፣ ኤዲ መርፊና ሮቢን ዊሊያምስ የሚሰሯቸውን ፊልሞች ተከታተል። ስትከታተል ግን ቀልዶቻቸውን ለመሸምደድ ሳይሆን ከማንኛውም ነገር እንዴት በተላሉ ቀልድ እንደሚፈጥሩ ዘዴውን ለመማር ይሁን። ቃላትን አጣመውና ሰንጥቀው እንዴት ቀልድ እንደሚፈጥሩባቸው ተመልከት።

ከዚህ በታች እኔ ራሴ የምጠቀምባቸውን ዘዴዎች ዝርዝርና እንዴት እንደምጠቀምባቸው እንይ።

1. ሰዎች ስሜታዊ የሆነ መልስ ሲሰጡ ካስተዋልኩ "ከምር ግን ይሔ እንዴት ሊሰማሽ ቻለ?" እላለሁ። ለምሳሌ አንዲት ሴት "ኡፍ ሰዎች አጠገቤ ሲያጨሱ ያስጠላኛል" ካለች "እንዴት እንደዚህ ሊሰማሽ ቻለ?" ብላት ምዕቱ ለጭስ ጠንከር ያለ ስሜት ማዳበር የቻልሽው እንዴት ነው? ሲጋራ በዚህ ርቀት ማሽተት የቻልሽበት ለየት ያለ ልምድ አለሽ? እንደማለት ነው።
2. "ለማንኛውም..." እልና ቶሎ ፊቴን ዞር አደርጋለሁ። ለምሳሌ አንዲት ሴት "እዛ ጋ ያለችው ልጅ አታስጠላም?" ብትል "አንቺ መስለሽኝ ነበርኮ! ለማንኛውም..." ብዬ በስሱ ፈገግ እልና ወደ ሌላ ቦታ ፊቴን አዞራለሁ። ወደ ሌላ ቦታ ማየቴና ጨዋታውን ለመቀየር የማደርገው ጥረት ያስቃታል።
3. ሴቶች የሚሉትን እያንዳንዱን ዓረፍተ ነገር አጣምማለሁ። በንቃት እከታተላለሁ። "ወደ ክለብ ሄደን ቢራ እንጠጣ" ስላት "እሺ እንደዛ እናድርግ" ብትለኝ "እናድርግ? እዚሁ እናድርግ ማለትሽ ነው? እዚህ እንኳን ወንበሩ በደንብ ለመንቀሳቀስ አይመቸንም። ከዚያ ይልቅ ውጭ ብንጠጣ ይሻላል" እላታለሁ።
4. ወሲባዊ ትንኮሳ እየተካሄደብኝ እንደሆነ በማስመሰል ደጋግሜ እከሳታለሁ። ለምሳሌ "በጣም እየደከመኝ ነው። አሁን የአልጋ ሰዓት ነው" ብትለኝ የምላት "ምን አልሽ? አልጋ ... ገና መሳም እንደምትችይ እንኳን ሳታረጋግጪ ወደ አልጋ ልትወስጂኝ ትፈልጊያለሽ? ሆይ ሆይ መጀመሪያ በደንብ መተዋወቅ የሚቀድምባቸው እነዚያ ዘመናት የት ገቡ?" ነው።

5. አጋንናለሁ። ወፍራም ሴት ባጠገባችን ስታልፍ ካየሁ "ገምቺ እስኪ ... 200 ኪሎ?" እላታለሁ። በሆነ አጋጣሚ ስለልብሷ ወይም ስለ ፀጉሯ ቅሬታ ስታቀርብ ካየሁ አሁንም አሁንም እየደጋገምሁ አነሳባታለሁ። "ፀጉሬ እንዴት ነው በደንብ አልተበጠረም አይደል?" ካለችኝ "በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም አስተያየት መስጠት አልፈልግም" እላታለሁ። ይሔ ጥሩ ቀልድ ነው። ብዙ ጊዜ ቀለል ያለ ምት ይከተለኛል። ከዚያም ቀኑን ሙሉ ስለ እርሷ ፀጉር እኔ መግቢያ ማጣቴን እያነሳሁ፤ ሰው ሁሉ ፀጉሯን በግርምት እንደሚያየው እያወራሁ፤ ከእርሷ ጋር መታየት እንዴት እንዳሳፈረኝ እየነገርሁ ስቀልድባት እውላለሁ።
6. በአካባቢዬ የሚገኙ ነገሮች ላይ ለመቀለድ እሞክራለሁ። ትልቅ መቀመጫ ያላት ሴት ባጠገባችን ካለፈች "ሙሉ ቂጦ እዚህ ቤት ውስጥ እየተንጎራደደች ነው" እላለሁ ጮክ ብዬ።
7. ብዙ አልስቅም። በተለይ ደግሞ በራሴ ቀልዶች አልስቀም። ምክንያቱም በራሴ ቀልዶች ከሳቅሁ የቀልዴን የማሳቅ ሃይል እቀንሰዋለሁ። ኮስተር ካልሁ ግን እንዳሳቀልኝ ትንሽ ይዘልቃል።

### "ጓደኞች እንሁን" ብሎ መጀመር

"Friendship often ends in love; but love in friendship – never."

Charles Caleb Colton

ሴቶች "እወደዋለሁ ግን እንደ ጓደኛ ብቻ ነው" ሲሉ ሰምተህ ታውቃለህ? አያናድዱህም? ይህ የእነሱ አንዱ ብልሃታቸው ነው። አሁን ለእኛ ለወንዶችም እንደሚያገለግለን አውቄያለሁ።

ሴት ልጅን አግኝቼ ትንሽ አዋራትና "ጓደኛ እንሆናለን" እና "ምንም ባይፈጠር እንኳን ጥሩ ጓደኛሞች እንሆናለን" የሚሉትን አባባሎች

እጠቀምባቸዋለሁ። ከዚያ በተከታዩ ቀጠሯችን ለምን ጓደኛ እንሆናለን እንዳልኩ አብራራላታለሁ። "አየሽ አንድን ሰው በደንብ ለማወቅ መጀመሪያ መሆን ያለበሽ ጓደኛ ነው" እላታለሁ። ከዚያ ጓደኝነታችን ሲጠናከር አንደጉድ እጀነጅናታለሁ። ወሲብ ነክ ወሬዎችንና ቀልዶቼን እቀጥላለሁ። ይህ ለእርሷ የሚያሳያት ነገር ቢኖር ራሴን የተቆጣጠርኩ ልጅ መሆኔንና ጓደኝነታችንንም ወደፊለግሁበት መቀየር የምችለው እኔ መሆኔን ነው። ይህ ደግሞ ምናልባትም አንዲት ሴት አጋጥሟት የማያውቅ ዓይነት ነገር ነው።

በነገራችን ላይ ጓደኛ ስለመሆን አስቀድመህ ካወራህላት ከመልኳ በዘለለ ውስጣዊ ባህርይዋን ብዙ ለማጥናትም ያግዝሃል። ያለበለዚያ በመልኳ ቆንጆ ስለሆነች ብቻ ዘው ብሎ መስመጥህ ከሚሊዮን የወንድ አልጫዎች በምን ይለይሃል? ንጹህ ጓደኝነት የሚለውን ነገር እስከዘላለሙ ልትጠብቀው ትችላለህ። እንዲያውም ወደ ፍቅር ግንኙነት ካመራችሁ በኋላም የጨዋታ መፍጠሪያ ሆኖ ያገለግልሃል።

ሁሉንም ዓይነት የስልክ ወሬዎችህንና ቀጠሮዎችህን ቀድመህ ጨርስ። ይህን በማድረግህ አስደሳች ምላሽ ታገኛለህ። ይህንን በሰው ላይ እንደመጫወት አትቁጠረው። እኔም ብሆን በሰው ጭንቅላት ላይ መጫወት ደስታን የሚሰጠኝ ሰው አይደለሁም። ነገር ግን ይህንን ነገር በአግባቡ ስትጠቀምበት ሴቶች ደስ ይላቸዋል። አዎን እነርሱ የሚያፈቅሩት አይነት ጨዋታ ነው። ሴቶች እኮ መወጣጠርን ይወዳሉ። የስልክ ንግግርህን፣ ወሬህን፣ ወዘተ ቀድመህ መጨረስ የሚኖርብህ ምክንያት ሁለት ስራዎችን ስለሚሰራልህ ነው። በመጀመሪያ "እኔ አልጓጓሁም ሌሎች የምሰራቸው ስራዎች አሉብኝ። ልታገኚኝ ከፈለግሽ በደንብ መታገል አለብሽ" የሚል አንድምታ ስለሚያጭር ነው። በሁለተኛ ደረጃ ነገሮችንና ሁኔታዎችን

የምትቆጣጠር ዓይነት ወንድ መሆንህን ያሳይልሃል። ይህንን ስልትህን በእያንዳንዷ የስልክ ጥሪና ንግግርህ እስከመጨረሻው ከተጠቀምክበት በምታገኘው ምላሽ በደስታ ትሰክራለህ። ሴቶቹ እንዲህ ሲሉህም ታዳምጣለህ "ምነው? ጥሩ ጊዜ እያሳለፍን ነው እኮ!"፣ "እሺ መቼ አገኝሃለሁ?"፣ "አትወደኝም እንዴ?"

በነገራችን ላይ እንደዚህ ማለት ሲጀምሩ ወጥመዳቸው ውስጥ እንዳትገባላቸው። እንዲህ በል "በእርግጥ እወድሻለሁ። ጥሩ ጊዜ እያሳለፍንም ነው። ግን ስራ በዝቶብኛል። የሆነ የምሰራው ሥራ አለኝ። ስለዚህ ነገ ደውይልኝ። ምናልባት በዚህ ሳምንት መጨረሻ ልንገናኝ እንችላለን" - እንዴት አንጀት የሚያርስ መልስ መሰለህ።

የሚገርምህ ሴቶቹም ይወዱታል። ጭካኔና ወጣ ያለ ቅጣት ቢመስልህም ሴቶች ዘወትር "ያፈቅረኛል? ይወደኛል? ይደውልልኛል?" መሰል ጥያቄዎች እየጠየቁ መኖርን ይፈልጉታል። አውቃለሁ ለማመን የሚያስቸግር እውነታ ነው። ግን እመን። ይህንኑ ምክር አልሳካ ላላቸው ወንዶች ነግሬአቸው ሳይቀበሉት የቀሩ ብዙ ናቸው። ይኼው ዛሬም ሴት ፍለጋ ከመኳተን ግን አልዳኑም። የሚሳካላቸውም አይመስለኝም። በጣም የሚጓጉ ወንዶች ስልክ ጆሯቸው ላይ ካልተዘጋባቸው ማውራት አያቋርጡም። ራሳቸውን ውድና ኩሩ ባለማድረጋቸው ውድነታቸውን ዋጋ ቢስ ሲያደርጉ ይኖራሉ። አንተ ግን ተመሳሳይ ስህተት እንዳትሰራ ተጠንቀቅ!

የእንክብካቤና የፍቅር ቃላቶችህን በቀጥታ አትጠቀምባቸው። ለምሳሌ እንኳን በቀን 12 ጊዜ "አንቺ እኮ ቆንጆ ነሽ" ማለት አስደሳችና ማራኪ አይደለም። ከዚያ ይልቅ ይህንኑ የሚገልፅ 3 ወይም 4 መስመር ግጥም ፅፈህ በቀላሉ ልታገኘው የምትችልበት ቦታ አጠገቧ ብትጥለውና በድንገት ከፍታ ብታነበው ድንገተኛና በጣም አስደሳች ይሆንላታል። በመጨረሻ ደግሞ ከሌት ልጅ የምታደንቅላት አንድ ድብቅ ነገር ካለ እርሱኑ አውጥተህ አውራላት። ሴቶች እያንዳንዷን ድብቅ ነገር ለይቶ የሚያወጣና የሚያደንቅ ወንድ የምር ይወዳሉ። ለምሳሌ ከእርሷ በጣም የሚያምረው ፀጉሯ ከሆነ አንተ ልታደንቅላት የሚገባህ አይኖቿን ወይንም ተረከዟን መሆን አለበት። ፀጉሯንማ ማንም መንገደኛም ሲያደንቅላት ስለሚውል ብዙም አይገርማትም። ጨርሻለሁ"

ሴቶች ስለእነርሱ ስታስብ ደስ ይላቸዋል። ስለዚህ በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ስለ እርስዋ ማሰብ አለማሰብህን ማረጋገጥ ትፈልጋለች። ይህንን ለማድረግ ደግሞ የተለያዩ መንገዶች ትጠቀማለች። ሴቶች ስጦታ ስትሰጣቸው አጥብቀው የሚደሰቱት ለሰጠሃቸው ዕቃ ልዩ ፍቅር ስላላቸው አይደለም። በፍጹም አይደለም። ስለእነርሱ ጊዜ ወስደህ ማሰብህንና ለእነርሱ ብለህ መግዛትህን ማረጋገጥ ስለሚፈልጉ ነው። በእርግጥ ይህ ለእኛ ለወንዶች ትርጉም የሚሰጥ ነገር አይደለም። ለአንተ ትርጉም ይሰጥሃል እንዴ? ለእኛ ግን አይሰጠንም። ግን እውነታው እንደዚያ ነው። ስለዚህ ለምትፈልጋት ሴት እንዳገኘሃት አብራህ ባልነበረችት ጊዜ ስታስታውሳት እንደነበር ግለፅላት። ተጠንቀቅ መግለፅ በቃላት ብቻ አይደለም! ይህንን ማድረግ ከቻልክ ደግሞ ስጦታ መግዛት አያስፈልግህም ማለት ነው።

ለምን ቢባል የስጦታ ዋናው ተግባር ስታስታውሳት እንደቆየህ መግለፅ ነውና!

ይሽውልህ ደግሞ አንድ የማይታመን ነገር ግን የማይታበል ሃቅ፡- ሌቶች እንቆቅልሽ ይወዳሉ። አደናጋሪ የሆነን ጨዋታ ሌቶች ይወዱታል። ይህ ማለት አንድን ነገር አንዴ በመከሳተር ሌላ ጊዜ ደግሞ እየተለድክ ስትሰራው ይወዱታል ወይንም በንግግርህ ጠንከር ብለህ በአካል አፍታሪ ሆነህ ስትገኝ ደስታ ይፈጥርላቸዋል። እየሳምካት "አልወድሽም" ስትላት ወይንም ውበቷን እያደነትህ ግን ደግሞ ፊትህን ብታኮስትር ቢታ ደስ ይላታል። ለምሳሌ ቁጭ ባለችበት እየሳምካት እጇን ይዘህ ካስነሳሃት በኋላ መቀመጫዋን ቸብ ብታደርገውና "በጣም ንዘዝ ላሚ መሆንሽን ለመግለጽ ነው" ብትላት ደስታዋ ወሰን አይኖረውም። ልብ በል ደስታ ሁሉ በላት አይገለፅም።

አንድ ሌላ ነገር ደግሞ እንጨምር። ሴት ልጅ ስለወሲብ ማውራት በጣም ትወዳለች። በርካታ ወንዶች በማያውቷት ሴት ፊት ስለወሲብ ማውራት ምቾት አይሰጣቸውም። እስኪ አጠገብህ ለተቀመጠች ሴት አንድ ሁለት ወሲብ ነክ ቀልዶች ንገራት ወይም ደግሞ በቴሌቭዥን ስላየኸው ወሲብ ነክ ፕሮራም አውራላት። ሊገርምህ ቢችልም ባልጠበቅኸው መልኩ የርዕሰ ወሬው ዋና ተዋናይት ሆና ታገኛታለህ።

ምንጊዜም የማይገመትና ያልተጠበቀ አይነት ሰው ሆኖ መገኘት አለብህ። በእርግጥ ከመጠን ያለፈ ወጣ ያለ ተግባር ችግር እንደሚያመጣ አንተም ታውቃለህ። በጥቅሉ ግን ሰው በተለይ ደግሞ ሌቶች ለየት ያለና አዲስ ነገር እንደሚወዱ እወቅ። ማወቅ ብቻም ሳይሆን ተጠቀምበት!

እንድትስማት ስትጠይቅህ እምቢ በላት። ግን ደግሞ ሳትረሳ ከቆይታዎች በኋላ አቅፈህ ሳማት። ጭንህ ላይ ልትቀመጥ ብትመጣ ከልከላት። ግን ትንሽ ቆይትህ እቅፍ አድርገህ ፍቅር ለግሳት። ገና እንዳገኘሃት የፈላጊነትህን ደወል ደጋግመህ ከደወልከው በቃ በራስህ እጅ በሩን እንደዘጋኸው ቁጠረው። ፍቅር ወይም ወሲብ የተራበ ሰው መስለህ ከቀረብካት ለአንተ ያላት ፍላጎት እንዲቀንስ እያደረግካት ነውና ጠንቀቅ በል! እንድትስማት ስትጠይቅህ እንኳን ልትስማት የምትችለው ጀርባህን ስታሻሽህ ብቻ እንደሆነ ንገራት። ቁም ነገሩ ምን መስለህ? - የጠበቀችውን ነገር ደብቅና ያላሰበችውን አዲስ ነገር ፈጥረህ ጠብቃት። ሁሌም አዲስ ነገር ፍለጋ አንተ ዘንድ ትመላለሳለች። አዲስ ነገር መፍጠር እንኳን ቢሳንህ አልፎ አልፎ ትርጉም የሌላቸው ነገሮች ማድረግን አትርሳ!

### *ሴቶች ወንዶችን የሚፈትኑባቸው መንገዶች*

ሴቶች በየአጋጣሚው ወንዶችን ሲፈትኑ ቆይተዋል። ወደፊትም ይቀጥላሉ። ይህ ባህርያቸው በተለያዩ መንገዶች ይገለፃል። ለምሳሌም በቅብጠት፣ በምሬት፣ አዲስ ነገር እንዲገዛላቸው በመጠየቅ፣ በማዘዝ፣ በመነጫነጭ እና በመሳሰሉት።

ለምሳሌ "ስማ የቴዲን ዘፈን እንዴት እንደምጠላው ብታውቅ እንዲያላዝንብኝ አትፈቅድም ነበር" ብትልህ "አሃ በቃ መኪናዬ ውስጥ መግባት አትፈልጊም ማለት ነው። ምክንያቱም ሌላ ዘፈን ላለመክፈት ወስኛለሁ" የሚለውን ዐረፍተ ነገር ቀልድ ይሁን የምር በማያስታውቅ ቅላፄ ብትለው አመፂ ቡን ይላል። ይህ ደግሞ ለእርሷ ግልፅ መልዕክት ያስተላልፍልሃል። በምንም አይነት መልኩ መቅበጥ ብትፈልግ የማያዳግም እርምጃ የመውሰድ አቅም እንዳለህ ያስረግጥልሃል። በዚህ ተናዳ ወይም

አኩርፋ ጥላ የምትሄድ እንዳይመስልህ። የለም! የለም! ቆራጥትህን ወዳው ሁልጊዜ ከጎንህ አትለይም! አንዳንድ ሴቶች በአደባባይ "አድርግ የተባለውን ሁሉ የሚፈፅም ወንድ ያስጠላኛል" ሲሉ ይደመጣሉ።

ከእንተ የሚጠበቀው አለመታዘዝ ነው። እንዲያውም በርካታ ሴቶች አዲስ ያገኙትን ወንድ እንደዚያ አይነት ፈተና መፈተን ይቀናቸዋል። ያዙታል፤ ያዘዙትን ሁሉ የሚፈጽም ከሆነ የወንድ አልጫ ማለት ያ ነው - ለእነርሱ። ስለዚህ አንተ ለዚህ አይነት ጥያቄ ምላሽህ "አሪፍ ነው" ብሎ በደንብ መሳቅ ይሁን። መሳቅህ "አሪፍ ነው" ማለትህ መፈተኛ መንገዷን እየቆረጥከው እንደሆነና ከምታስበው በላይ ተፈታታኝ መሆንህን ያሳውቃታል።

### *ሴቶችን የሚያማልላቸው ድምጽ*

ሴት ልጅ ወፈር ያለ የሚያስተጋባ እንዲሁም ደስ የሚል ሙዚቃዊ ቃና ያለው ድምፅ ትወዳለች። ያ ማለት ግን በጣም ቀጭን አልያም የሚልጎመጎም ድምፅ ካለህ በቃ ተስፋ የለህም ማለት አይደለም። ትኩረት ስጥተህ እስከተለማመድህ ድረስ ማሻሻል ትችላለህ። ስለዚህ በዚህም ጉዳይ ጠንክረህ ስራ!

*ሴቶች የሚወዱት ድምፅ እንዲኖርህ ከፈለግህ፦*

ድምፅ በአፍንጫህ እየወጣ ያስቸግርሃል የመካከለኛና ሴባ ጣቶችህን "V" ቅርፅ አስርተህ አፍንጫህን ደግፈውና ተናገር። በመንቀጥቀጥ ይለማሃል? አሁን ደግሞ ታችኛውን የአንትህን ክፍል በጣቶችህ ደግፍና ተናገር። አፍንጫህ ከጉሮሮህ የበለጠ የሚንቀጠቀጥ ከሆነ በተገቢው መንገድ እየተነፈስክ አይደለም ማለት ነው። ስለዚህ አየር ወደ ውስጥ ስታስገባ በአፍንጫህ ብቻ ስታስወጣ ደግሞ በአፍህ ብቻ ሆኖ ጨጓራህ

ወደላይና ወደታች ሳይሆን ወደውጭና ወደውስጥ እንዲንቀሳቀስ አድርግ። ጉሮሮህ እያደረግህ በመናገር ተለማመድ።

ድምፅህን አንተ የምትሰማበትና ሌሎች የሚሰሙበት መንገድ ይለያያል። ድምፅህ ለአንተ የሚደርሰው በጭንቅላትህ ግድግዳ በኩል ነው። ስለዚህ ሌሎች የሚሰሙትን ድምፅህን ለማወቅ በካሴት ቅዳና አዳምጠው።

ረጋ ብለህ መናገር ልመድ። ስትፈጥን ድምፅህ እየቀጠነ ይሄዳል። አፍህን በደንብ ክፈት። "እም" የሚለውን ድምፅ ደጋግመህ በማለት ተለማመድ። ጉሮሮህ ፈታ እንዲል አድርግ።

በምትናገርበት ወቅት ቀጥ ብለህ ቁም ወይም ተቀመጥ። ይህ የአተነፋፈስ ስርዓትህ ትክክለኛውን አቅጣጫ እንዲይዝ ያደርግልሃል። ከዚህም በተጨማሪ በራስ መተማመንህን የሚያጎላው ሲሆን የምትናገረው ነገርም የበለጠ ታማኝ እንዲሆን ያግዝሃል።

ግጥሞችን፣ መነባንቦችን ወይም የሚመችህን መጽሐፍ ጮክ ብለህ እያነበብክ ተለማመድ።

ከንግግሮችህ በፊት ውሃ ጠጣ። ቡና አፍ ያደርቃል። የብርቱካን ጭማቂ ጉሮሮ ያጎነትራል። ወተትና የወተ ተዋፅኦዎች ግግር ምራቅ ይፈጥራሉ። ለስላሳ መጠጥ ጋዝ ያበዛል።

ንግግርህን ለማጣፈጥ፦

- ❖ በቀላሉ የሚገቡ ገላጭ ቃላትን ተጠቀም።
- ❖ መደበኛ ያልሆኑ ቃላትን አስወግድ።
- ❖ በየጣልቃው ንግግርህን ገታ አድርግ።

- የምታናግራትን ሴት በስሟ አዋራት እንጅ "ማር" "ቆንጆ" እና የመሳሰሉ ቃላትን ከማለት ተቆጠብ። አልፎ አልፎ እጆችህን ነገር ለማጠንከር ተጠቀምባቸው።
- የምታናግራትን ሴት አይን ተመልከት። ማፍጠጥ ግን የለብህም።

*ፅናት*

ሴት ልጅ ሰባት ጊዜ "እምቢ" ብላ በስምንተኛው "እሺ" ልትልህ ትችላለች። ሴቶች እምቢታን ተፈላጊነታቸውን ለመጨመር የሚጠቀሙበት ጭምብል ነው። ለምሳሌ ገና በጠዋቱ ፍቅረኛህ "ዛሬ ማታ ወሲብ አናደርግም" ብትልህ እንደወረደ አስበህ እንዳትቀበለው። ይልቁንም ስሜቷ እየተፈታተናት መሆኑንና በአንተ ገፋፊነት እንደምትፈፅሙት ማሰብ መፈለጓን መግለጫ መንገዷ መሆኑን እወቅላት። የሚባለው እየገባህ ነው? ታዲያ ይህ ማለት አንዲት ሴት ስትነካካት "እረፍ" ብትልህ "አስገድደህ ድፈረኝ" ማለቷ ነው የሚል አቋም እንዳታዳብር አደራ!

*መመለስ የማትፈልጋቸውን ጥያቄዎች እንዴት ትመልሳለህ?*

ሴቶች ብዙ ጊዜ ወንዶች መመለስ የማይፈልጓቸውን አይነት ጥያቄዎች መጠየቅ ያበዛሉ። ይህ ደግሞ የትኛዋም ሴት ጋር ብትሄድ የማይቀርልህ ጉዳይ ነው። ስለዚህ አስቀድመህ ራስህን ታዘጋጅ ዘንድ ግድ ይልሃል።

"ማንን እያየህ ነው?"

"ስለጋብቻ ምን ታስባለህ?"

"ትወደኛለህ?"

"ይኼ ሱሪ ወፍራም ያስመስለኛል አይደል?"

እና የመሳሰሉ ብዙ መመለስ የማትፈልጋቸው ጥያቄዎች ይቀርቡልሃል። ለጥያቄዎቿ ተገቢውን መልስ (መስማት የምትፈልገውን መልስ) በመስጠት መልስላት። እንዴት?

"ያቺን ሴት እያየህ ነው አይደል?" ስትልህ

"አይ! ሌላ ሰው እያየሁ ነው"

"ትወደኛለህ?" ስትልህ

"በእርግጥ እንደ ጓደኛ እወድሻለሁ"

"ትናንትና ማታ ስደውል የት ነበርክ?" ስትልህ

"እ! ቤት ነበርኩ ትደውያለሽ ብዬ ጠብቄ ነበር። ስትዘገይ ጭፈራ ቤት ሄጄ ከብዙ ሴቶች ጋር ስደንስ አመሸሁ።"

"እኔ እኮ የምሬን ነው" ብትልህ

"ቤት ቁጭ ብዬ ነበር አልኩ እኮ፤ እሺ በቃ ከሌላ ሴት ጋር እየተዝናናሁ ነበር። አሁን ደስ አለሽ?" በቃ ከሆነ ጊዜ በኋላ እንደዚያ አይነት ጥያቄ መጠየቅ እርግፍ አድርጋ ትተዋለች። እዚህ ላይ ስትናገር የመቆጣት ወይም የመናደድ ስሜት ማሳየት እንደሌለብህ እወቅ! ሴቶች ነገር በቀላሉ ይገባቸዋል። ሊሰሙት የማይፈልጉት መልስ ማዘጋጀትህን ካወቁ በድጋሚ አይጠይቁህም። በቃ ይኼው ነው።

## ምዕራፍ አምስት

## ሴቶችና የስውነት እንቅስቃሴ ቋንቋዎቻቸው

ብዙ ወንዶች በርካታ አስቂኝ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ። "ምን ብላት ነው የበለጠ ልትወደኝ የምትችለው?" ፣ "እንደዚህ ካለችኝ ምን ልበላት?" እና የመሳሰሉ። ለሴቶች እኮ የቃላት ምልልስ ሁለተኛ ቋንቋቸው ነው። ሌላ በፍጥነት የመመለሻ መንገድ ሲጠፋ የሚጠቀሙበት ነው። ስለዚህ ወንዶች በቅድሚያ ልንገነዘብ የሚገባን ነገር ከቃላቶቻችን ይልቅ ተግባሮቻችን በሴቶች ዘንድ የበለጠ ተፅዕኖ እንዳላቸው ነው። ሌላው ይቅርና በወንዶችም ሆነ በሴቶች መካከል ከሚካሄዱ የመግባባት ጥረቶች ውስጥ በቃላት የሚተላለፈው መልዕክት ከአጠቃላዩ 7 ፐርሰንቱ ብቻ ሲሆን ቀሪው 93 ፐርሰንት መልዕክት ግን በምልክት /በስውነት እንቅስቃሴዎች/ እና በድምፅ ቅላፄ አማካኝነት የሚተላለፍ መሆኑን የቅርብ ጊዜ ጥናቶች አስረግጠዋል። አሁን ጥያቄዎችህ ሊወገዱ ይገባል። ከሴት ልጅ ጋር መግባባት ስትሻ ከፍተኛ የመግለፅ አቅም ያላቸው የስውነት እንቅስቃሴዎችህና የድምፅህ ቅላፄ መሆናቸውን ልብ በል።

### *የስውነት እንቅስቃሴዎች እና አጠቃቀማቸው*

አብዛኞቹ ወንዶች ሴቶች ከወንዶች የተሻለ የምልክት ቋንቋ እንደሚረዱ ይስማማሉ። በእርግጥም ሴቶች ስሜታችንን ከስውታችን እንቅስቃሴዎች አብጠርጥረው መረዳት ይችላሉ። እስኪ አንዲት የምትቀርባትን ሴት ወደ እርሷ እየተመለከተ ያለን ልጅ ጠቁምና ስለጉዳዩ እንድታብራራልህ ጠይቃት። የምትነግርህ ዝርዝር ጉዳዮች ባይገቡህም እንኳን በጣም የሚያስገርመህ ይሆናሉ። እንግዲህ ሴቶች የምልክት ቋንቋዎችን በቀላሉ የሚረዱ መሆኑን ካወቅህ ምልክቶችህ ትክክለኛውን

መልዕክትህን እንዲያደርሱልህ ማድረግ ደግሞ ያንተ የቤት ሥራ ነው ማለት ነው።

ካነበብናቸው የሥነ-ልቦና ጽሑፎችም ሆነ በዕለት ተዕለት የኑሮ ሂደት ካጋጠሙንና ካስተዋልናቸው ሃቶች ተነስተን ስናየው ሴቶች ለልበ ሙሉና ቀብራራ ወንዶች በቀላሉ ይረታሉ። በርካታ ሴቶች ቀብራራ ወንዶች እንደማይመቿቸውና በምንም መልኩ ከእነርሱ ጋር በፍቅር እንደማይጣመሩ ሊያወሩ ስምተህ ሊሆን ይችላል። እውነታው ግን ሴቶች እምቢ ሊሉት የማይቻላቸው ወንድ ከተጫዋችነቱ ጋ መጠነኛ ኩራት የጨመረውን ነው። ታዲያ አንተ በራስ መተማመን በውስጥህ መኖሩን የሰውነትህን እንቅስቃሴ በመጠቀም ለአንዲት ሴት የምትገልፅላት በምን መልኩ ነው?

በመጀመሪያ ደረጃ ምንጊዜም ቀጥ ብለህ ተራመድ። በምትራመድበት ወቅት ራስህን ቀና አድርግ፣ ትከሻህንም ወደኋላ ያዝ አድርገው። እርምጃህ ቀስተኛና የተመጠነ ይሁን። በመንገድ ላይ ከሴት ልጅ አይን ለአይን በምትተያይበት ጊዜ እርሷ ሳትሰብር አይንህን አትስበር። ምንም ቢሆን እርሷ ከመዞሯ በፊት አትዙር። በተጨማሪም ቅንድብህን ወደላይ ማንሳትም መልካም ነው። በተለይ ደግሞ አረማመድህ፣ የአንገትህ አሃዛር እንዲሁም አይንህ የሚርገበገብበት ፍጥነት ሙሉ በሙሉ በቁጥጥርህ ስር መሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባሃል። በምትቀመጥበት ጊዜ ጭብጥብጥ ብለህ አትቀመጥ እንዲያውም እጆችህንና እግሮችህን አታጣምር። እግሮችህን ከፊት አድርገህ ዘርጋ ብለህ ተቀመጥ። በተቻለህ መጠን ወደኋላ ተደገፍ እንጂ ወደፊት አታዘንብል ወይም ጠረጴዛ ተደግፈህ አትቀመጥ። አሁን የተባሉት ነገሮች ሲታዩ ምናልባት ለውጥ የሚያመጡ ላይመስልህ

ይችላል። ነገር ግን በአግባቡ ከተገበርካቸው ውጤቱን ለማየት ረዥም ጊዜ መጠበቅ አይኖርብህም። ሴቶች ጉጉነትን፣ አለመረጋጋትንና በራስ አለመተማመንን በቀላሉ ለይቶ የሚያውቅ ተፈጥሮ አላቸው። አንዲት ሴት ውስጧ በራስህ መተማመንህን አምኖ ከተቀበለ የበለጠ ወደ አንተ ከመሳብ በስተቀር ምንም ልታደርግ እንደማትችል ይሰማታል። በራስ የመተማመን ምሳሌ ከፈለግህ የጀምስ ቦንድን ፊልሞች ተመልከት! ጀምስ ፈገግ የሚለው አልፎ አልፎ እንደሆነና ስቆ እንደማያውቅ ታስተውላለህ። ከእርሱ በርካታ ነገሮች ልትማር ትችላለህ። በራስ መተማመንህን ልትገልፅ የምትችልበት ሌላ መንገድ በምታወራበት ጊዜ ንግግርህን ገታ ማድረግ በመልመድ ሊሆን ይችላል። በተለይ ደግሞ ንግግርህን ቆም በምታደርግበት ጊዜ ፊትህ ኮስታራነት እንዲታይበት ማድረግ የምትችል ከሆነ በእርግጥም አካባቢውን መቆጣጠር ችለሃል። ለምሳሌ "እኔም በአንቺ ቦታ ብሆን ኖሮ የምላት አሁን የምታስቢውን ነገር ነበር" የሚለውን "እኔም (ቆም) በአንቺ ቦታ ብሆን ኖሮ (ቆም አድርገህ ዓይኗን እየተመለከትህ) የምላት አሁን የምታስቢውን ነገር ነበር" በሚለው ልትተካው ትችላለህ። አየህ ላይ ላዩን እያወራህላት ያለው ስለ አርዕስተ ወሬው ቢሆንም ውስጥ ውስጡን ግን በራስ መተማመንን፣ ልብ ማንጠልጠልን እና ምስጢርን ነው እያወራህላት ያለኸው። በተዋጣለት የድምፅ ለዛና የሰውነት እንቅስቃሴ ስሜትህን መግለጽ ብትማር ስለ አየሩ ፀባይ ወይም ሌሎች የተለያዩ ተራ ነገሮች እያወራህ እንኳ ሴት ልጅ በወሬህ ተመስጣ እንድትቆይ ማድረግ ትችላለህ። ቁልፉ ጉዳይ ደግሞ በንግግርህ ጣልቃ ቆም ማድረግን አለመርሳትህ ይሆናል። ሁሌም ባይሆን በንግግርህ መሃል ቆም በል። ይሔ ንግግርህ የሚስብ እንዲሆን ያደርጋል።

## ሴት ልጅ የፈለገችህ መሆኗን የምትገልፅባቸው መንገዶች

ስለሴቶች ባህሪያት የተፃፉ በርካታ መጽሐፍት እንደሚሉት አንዲት ሴት በምታወራበት ጊዜ አንገቷን ወደ አንድ ወገን ካዘነበለች፣ ከንፈሯን ከላሰች፣ ፀጉሯን ካስተካከለች እንዲሁም በትከሻዋ አሻግራ ከተመለከተችህ በአንተ ላይ ፍላጎት ስለማሳደሯ 67 ፐርሰንት እድል አለ። ለማንኛውም ቁምነገሩ ያለው ልጅቱ ከአንተ ጋር ባለችበት ጊዜ ምን ያህል የጓደኝነት ስሜት አሳይታለች የሚለው ላይ ነው። እርግጥ ነው አሁን አሁን አንዳንድ ሴቶች ከሌሎች በበለጠ ግልፅ ናቸው። በአጠቃላይ ግን በቆይታችሁ ወቅት ነፃ ከሆነችና ደስ የሚሉ ወሬዎችን በቀላሉ ማንሸራሸር ከቻላችሁ በጨዋታው ጥሩ ውጤት እያስመዘገብህ መሆኑን ትረዳለህ። በዚህ ጊዜ ከአንተ የሚጠበቀው ወደፊት መግፋት ነው። ይህ ትንሽ ማብራሪያ ያስፈልገዋል። ለምሳሌ ንግግራችሁ ጥሩ እየሄደ ከሆነ ስልክ ቁጥር ጠይቅ። እየተጨዋወታችሁ አየር ለመውሰድ ከወጣችሁና ነገሮች መልካም አካሄድ የተከተሉ ሲመስልህ ተጠጋና ሳማት። ቤትህ ውስጥ ፊልም እያያችሁ ስትስማት ከቆየህ እጇን ያዝና ወደመኝታ ክፍልህ ምራት። ሁልጊዜም ወደሚቀጥለው ደረጃ መሻገርን አትርሳ! ሴቶች ይህንን ካንተ የሚጠብቁት ጉዳይ ነው። ካልተመቻቸው እነርሱ ያስቆሙሃል። ነገር ግን በመጨናነቅ አታድርገው። በዕድሉ ተጠቀም። አታስገድድ ግን ወደፊት ቀጥል!

ሴት ልጅ መደባበስና መነካካትን ትወዳለች። ከሴት ልጅ ጋር በምታወራበት ጊዜ (በአካልም ሆነ በስልክ) ስለመተሻሸት፣ ስለመሳሳም እና መነካካት ያለህን ጥልቅ ፍላጎት እንዲያውም እነዚህን ነገሮች ሌሊቱን ሙሉ ስትፈፅም ማደር እንደሚያስደስትህ ብታወጋት ፊቷ ሲለዋወጥ ማየትና እንደፈለገችህ መረዳት ትችላለህ። በወሬህ ጣልቃ ስለ መተሻሸትና መተቃቀፍ ብታወራ፣ "እንገትሽ አካባቢ ጣቶቼን በትከሻሽ ላይ ማንሸራሸር በጣም ደስ ይለኛል" ብትላት ውጤቱን በደቂቃዎች ውስጥ ታየዋለህ።

## ክፍል ሦስት

## የሴት ልጅን ልብ በፍቅር ማንበርከክ

### ምዕራፍ ስድስት

### ሴትን ለማስደሰት ምን ማድረግ አለብህ?

አንዳንድ ሰዎች "ሴት ልጅ ቤቱ ካላማረና አልጋዬ ካልተንቦጠቦጠ እንደማትተኛልኝ አውቃለሁ" ሲሉ ይደመጣሉ። የሚሉት ነገር ሙሉ ለሙሉም ባይሆን እውነትነት አለው። ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ጭንቅላታቸው ውስጥ ስለሴትን የሚያስቡትን ያህል በተግባርም ስለኪታማ መሆን እንደሚችሉ መዘንጋት አልነበረባቸውም። ነገሮች እንደሚሳኩና እንደማይሳኩ ለማወቅ አንድም ከአሁን በፊት ከሞከረ ሰው ልምድ መቅሰም ያስፈልጋል አልያም ሞክሮ ማየት ይገባል።

### ተዘጋጅቶ መጠበቅ

ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ነገሮች ስለሴትህን የሚያፋጭ ናቸውና ችላ አትበላቸው።

1. መኖሪያ ቤትህ የተደራጀና ንፁህ ይሁን።
2. አልጋህ የተነጠፈ፣ አንሶላዎቹም ንፁህ ይሁኑ።
3. የሚጠጣ ነገር (አልኮል ያለውም ይሁን የሌለው) ይኑርህ - እንግዶች በመጡብህ ጊዜ በቀላሉ ትጋብዛቸዋለህ።
4. መጠባበቂያ ይኑርህ (ገንዘብ፣ ምግብ ... ወዘተ)።

ቤትህ እንግዳ ለመቀበል የተዘጋጀ እስካልሆነ ድረስ ከሴት ልጅ ጋር የሚኖርህ ግንኙነትም የተሳካ አይሆንም። ከአንዲት ሴት ጋር ቀጠሮ በሚኖርህ ጊዜ ቤትህ ወይም መኪናህ ውስጥ እንከን ሊፈጥር የሚችል ነገር አለመኖሩን ማረጋገጥ ይጠበቅብሃል።

ቀጥለን ከሌሎቹ ወንዶች በምን ለየት ብለህ መታየትና የምትፈልጋትን ሴት መሳብ እንደምትችል እንነጋገር፡-

## ቤት ውስጥ ምግብ ማብሰል መማር

ወጪ ቆጣቢ መሆኑ፣ ባሻህ ጊዜ የፈለግኸውን አማርጠህ መብላት መቻልህ፣ የሚወስድብህ ጊዜ ትንሽ መሆኑ፣ ምርጫ የምታውቅ ወንድ መሆንህን ስለሚገልፅ እና ሌሎች በርካታ ጥቅሞች አሉት - ቤት ውስጥ ማብሰል መቻል። የበለጠ መሻሻል ቢያስፈልግህ ደግሞ አንድ የምግብ አበላሰል መጽሐፍ ብትገዛ በቂህ ይሆናል። ታዲያ ይህ በቀላል ወጪ የምታዘጋጀው ምግብ የፍትር ማጣፈጫ ቅመም ሆኖ ሊያገለግልህ ይችላል። አንተ ያዘጋጀኸው ምግብ እንደሆነና ለእርሷ ብለህ እንዳዘጋጀኸው ብትገልጽላት ደግሞ የምትለጥህ ነጥብ በእጅጉ ከፍ ይላል። ከዚያ በኋላ በስልክም ሆነ በአካል ስታገኛት "አንድ ጥሩ ሃሳብ አለኝ። የምወደውን ፓስታ ለማዘጋት ተፍ ተፍ እያልኩ ነበር። ለምን ቤት አትመጪምና ላንቺም አላዘጋጅልሽም?" በሚል ዕድሉን ልትጠቀምበት ትችላለህ። ይህንኑ ዘዴ አዲስ ለምትተዋወቃት ሴት እንኳን ልትጠቀምበት ትችላለህ።

## ሴቶች የሚወዷቸው ጥበቦች

ሴቶች በተፈጥሯቸው ኮከብ ቆጠራ፣ ካርድ መጣል፣ መዳፍ ማንበብ፣ የእጅ ጽሑፍ አጣጣል ትንታኔ፣ ሳይኪክ እና የመሳሰሉትን ወንዶች ብዙም ትኩረት የማይሰጧቸውን ጥበቦች በጣም ይወዷቸዋል። ስለዚህ ጊዜ ወስደህ ስለነዚህ ነገሮች የሚያወሩ መጽሐፍትን አንብብ። ከአንዲት ሴት ጋር በምታወራበት ጊዜ ድንገት እጇን ሳብ አድርገህ ውስጥ መዳፏን ትንሽ ካስተዋልህ በኋላ "ዋው! ደስ የሚለው ተፈጥሮ ያለሽ ልጅ ነሽ ባክሽ" ብትላት ውስጧ ይቁነጠነጣል። ከአንተ የተለየ ጥበብ እንደምታገኝ ታስባለች። ከአንተ ጋር የምታሳልፈው ጊዜም እንዲበዛ ትመኛለች። መዳፏን በማንበብ ሂደት ደግሞ መልዕክት አዘል የእጅ

ማላጅህን መቀጠል የምትችልበትን አጋጣሚ ታመቻቻለህ። ለዚህ ጉዳይ እንዲያግዝህ አንድ ወይም ሁለት የማሳጅ ትምህርት መጽሐፍትን ማንበብ ብትችል የበለጠ ተጠቃሚ ትሆናለህ።

## ርዕሰ ወሬ ማዘጋጀት

የውይይት ርዕሶችን ማዘጋጀት በአብዛኛው የወንዶች ስራ ነው። በአጠገባችሁ የምታልፍ በጣም ወፍራም ሴት ፊት ለፊት የተተከለ ታፔላ፣ የቤቱ አሰራር በአጠቃላይ በአካባቢው የሚገኝ ማንኛውም ነገር የወሬ ርዕስ ሊሆን ይችላል። ከአንተ የሚጠበቀው ርዕሱን ወደ መድረክ አምጥቶ አስተያየት እንድትሰጥበት መጋበዝ ይሆናል። በተለይ ደግሞ ቤትህ ይዘሃት የምትሄድ ከሆነ ለየት ያሉና የሴት ልጅን ትኩረት ሊስቡ የሚችሉ ዕቃዎችና መጽሐፍትን ማዘጋጀት ብልህነት ነው።

በተለይ በተለይ ሴቶች የሚወዷቸውን አይነት ርዕሶች የያዙ መጽሐፍት፣ መጽሔቶችና ጋዜጦች መደርደሪያህ ውስጥ ቦታ ብትሰጣቸው ብድራቸውን በተገቢው መልኩ ይከፍሉሃል። ስለፍቅር፣ ወሲብ፣ ፋሽን ወይም ደግሞ ስለኮከብ ቆጠራ አልያም መዳፍ ማንበብ የሚያወሩ መጽሐፍትን በቀላሉ በሚታዩበት ቦታ ማስቀመጥ ጥቅም አለው። በጣም ቀልብ የሚገዛ የሚመስልህን መጽሐፍ ደግሞ ጠረጴዛህ ላይ ጣል ብታደርገው በቀላሉ ብድግ አድርጋ እንድትመለከተውና የመወያያ ርዕስ እንድታመጣ ያግዛታል።

አንዳንድ ቀላል የሚባሉ በሳንቲምና በካርታ የሚሰሩ ተአምራትን መማር ጠቀሜታው የጎላ ነው። አጭር ጊዜ ወስደህ ያዳበርካቸው እነዚህ ጥበቦች እንስቷን እጅጉን የምታስደስምበትንና ዳጎስ ያለ አድናቆት የምታተርፍበትን መንገድ ይከፍቱልሃል።

## ሴት ልጅን መንከባከብ

ሴት ልጅ በተፈጥሮዋ እንክብካቤ ትወዳለች። አንተም ከእርሷ ጋር እስካለህ ድረስ ልትሰጣት የሚገቡ ክብርና እንክብካቤዎች አሉ። ከዚህ በታች የተወሰኑትን ለመዘርዘር ተሞክሯል። እንደ አስፈላጊነታቸው እያጣጣምህ ተጠቀምባቸው፡-

- ከፊት በመቅደም በርና መስኮት መክፈት ያንተ ድርሻ ይሁን። ይህ በጣም ያስደስታታል።
- መቀመጥ ስትፈልጉ ከፊቷ ቅደምና ወንበር ስበህ አስቀምጣት።
- በመንገድ ዳር ስትሄዱ ሁሉጊዜም በመኪኖቹ በኩል ያለውን ጎን ተጠቀም። ለምን እንደዚያ እንደምታደርግ ይገባታል። አስፈላጊ ከሆነ ደግሞ ምናልባት መኪና መንገዱን ስቶ ቢመጣ እርሷን ከልለህ ራስህን መስዋዕት ለማድረግ ማቀድህን አስረዳት። ምንጊዜም ቢሆን ሴቶች ለምትሰጣቸው ሽፋንና እንትስቃሴ ሁሉ ነጥብ ይይዙልሃል። አሁን እንዲህ በቀላል ወጪና ጉልበት የሴትን ልጅ ቀልብ መግዛት እንዴት እንደሚቻል ገባህ አይደል

### *ሴት ልጅን በፍቅር ለመማረክ ማዳበር ያለብህ አምስቱ ክህሎቶች*

1. ተረበኛና ጅንን መሆን፡- ሴቶች እንዲወዱህ ከፈለግህ ተረበኛ መሆን አለብህ። አንተ ካጠገባቸው እስካለህ ድረስ የደስታ ስሜት እንዲማቸው ማድረግ እንደምትችል ማሳየት አለብህ። ለምሳሌ ፈጠን ፈጠን እያለች የምታወራን ልጅ ለጓደኛቿ "ቆይ ይህች ልጅ ወሬዋን የምትጨርሰው መቼ ነው?" ወይም "ይህች ልጅ ሁሌም እንደዚህ አማራሪ ናት እንዴ?" የሚል ተረብ ጣል ማድረግ የተለየ ትኩረት ያስገኝልሃል። ለየት ያለና "ጋጠ ወጥ" አስተያየቶችን የሚሰጥ ሰው በሰዎች ጭንቅላት ውስጥ

በቀላሉ ይቀረፃል። ምክንያቱም የሰው ኑሮ ድግግሞሽ ሆኗል። ጠዋት ከመኝታዋ ትነሳለች። አልጋዋ ያው የተለመደው ነው። መኖሪያ ቤቷ የበፊቱ ነው። ወደ ስራ ቦታ የምትሄድበት መንገድ አልተቀየረም። ስራ ቦታ የምታገኛቸው ሰዎች የተለመዱና ተመሳሳይ ጨዋታ የሚጫወቱ ናቸው። ብቻ ሁሉም ነገር ስለሚደጋገም አሰልቺ ሆኖባታል። ስለዚህ እርሷ የምትፈልገው አዲስ ነገር ነው። ያን አዲስ ነገር መፍጠር መቻል ነው እንግዲህ ካንተ የሚጠበቀው። ያልተለመደ፣ የሚያስቅ፣የሚገርም ነገር ማድረግ አለብህ። ያኔ ሴቶቹ ደግመው ሊያዩህ ይፈልጋሉ። ከእርሱም አልፈው ለሌሎች ጓደኞቻቸው ሊያሳዩህ ይፈልጋሉ።

2. **መሳጭ ታሪክ ማውራት መቻል፡-** መሳጭ ታሪክ ለማውራት ጦር ሜዳ ሄዶ መምጣት ወይም ራስ ዳሽን ተራራን መውጣት አይጠበቅብህም። ዋናው ነገር ታሪኩን የምታቀርብበት መንገድ ነው። አድማጮችህን እንዴት መመሰጥ እንደምትችል መማር አለብህ። የአነጋገርህን ለዛና የድምፅህን ቃና አሻሽለህ ሰዎች በዙሪያህ ተኮልኩለው ሊያዳምጡህ የሚወዱ ዓይነት ወንድ ሁን።

3. **ራስን ችሎ መቆም፡-** ሴት ልጅ ጥገኛ ወንድ አትወድም። ያለምንም እርዳታ ራስህን ችለህ መቆም እንደምትችል ማወቅ ትፈልጋለች። እርሷ የምትፈልገው በራስህ ዛቢያ የምትሸከረከር እንድትሆንላት፣ በስበትህ አሸንፈህ እንድትወስዳት፣ ወስደህም በዚያው እንድታስቀራት ነው። በዛቢያህ አብራ እንድትሸከረከር የሚያደርጋት "የሚከተለው ምን ይሆናል?" የሚለው ውጥረት ነው።

ሳትፈራ እየተረብክ በጓደኛቿ ፊት አስቅባት። ጥሩ ቀልድ ተናግረህ ሁሉም እየሳቀ ባለበት ሁኔታ አንተ ትተሃቸው ሂድ። ይህ አንተ

የራስህ ዓለም ያለህና ከእነርሱ ጋር ከመሆን የተሻለ የምትሰራው ስራ እንዳለ ይገልጽልሃል። እንድትቆይና እንድትጫወት ቢወተውቱህ እንኳን መሄድ እንዳለብህ ንገራቸውና ሂድ። ይህ በጣም እንድትፈልግህ ከመፈለግም አልፋ እንድታሳድድህ ያደርጋታል። ወርቃማ የስበት ህግ ይሏል ይህ ነው።

4. ከመለፍለፍ መቆጠብ፦ ብታምንም ባታምንም ሁልጊዜም ባይሆን ዝም ማለት ትልቅ ችሎታ ነው። ሰዎች በተለይም ሴቶች ታሪካቸውን የሚያዳምጣቸው ሰው በጣም ይፈልጋሉ። የተሰማቸውን እንዲያወሩ ጊዜ ስጣቸውና አስተያየትህን ከመስጠትህ በፊት ለአፍታ ፀጥ በማለት ልባቸውን አንጠልጥለው። ከአፍታ ዝምታ በኋላ የሚያረካ መልስ ስትሰጣቸው ያኔ በአንተ ላይ ያላቸው እምነት እጅጉን ይጠነክራል።
5. ምልክቶችን ማንበብ፦ ከሁሉም ይበልጥ ልትካንበት የሚገባህ ቁልፍ ከህሎት ምልክቶችን ማንበብ ነው። ሴት ልጅ መውደዷን፣ መጥላቷን፣ መሄድ መፈለጓን፣ መሳም እንዳለኛት፣ ወሲብ እንዳማራት እና ሌሎች ፍላጎቶቿን በዋናነት የምትገልፀው በምልክት ነው። ስሜቷን ከእንቅስቃሴዎቿ መረዳት ካልቻልክ ነገሮችን ልታበላሻቸው ትችላለህ።

ሴት ልጅ እንድትማረክልህ ከፈለግህ ምልክቶቿን መተርጎም ተማር። ከዚህ በታች ሴት ልጅ በአንተ ላይ ፍላጎት እንዳደረባት የምታውቅባቸው 13 ምልክቶች ተዘርዝረዋል።

1. ከንፈሯን ትነክሳለች፣ ትልሳለች ወይም ምላሷን በፊት ጥርሶቿ ላይ ታንከባልላለች።
2. ጉንጯን ትነካካለች።

3. ከእንተ ጋር እያወራች የምትጠጣበትን ብርጭቆ በአውራ ጣቷና በሌባ ጣቷ ወደላይና ወደ ታች ትዳብሳለች።
4. የአይኗ ብሌን ስፋቱ ይጨምራል።
5. ጥርሶቿ ተከፍተው ፈታ ያለ ፈገግታ ታሳያሃለች።
6. እግሮቿን አጣምራ ከተቀመጠች ከላይ የተጫነው እግር ወዳንተ ይዞራል ወይም ወዳንተ አትጣጫ ወደፊትና ወደኋላ ይወዛወዛል።
7. የምታጨስ ከሆነ ጭሱን ወዳንተ በከንፈሮቿ መሃል ትልከዋለች።
8. በወሬ መሃል በአይኗ ትጠቅስሃለች።
9. ጡቶቿን የሚያጋልጥ ልብስ ከለበሰች ከእንተ ጋር እያወራች የጡቶቿ ጫፎች ይቀላሉ። (ወደ ጡቶቿ አፍጥጠህ ስታይ እንዳትያዝ ተጠንቀቅ)
10. ፊቷን ሙሉ በሙሉ ወዳንተ አዙራ ትቀመጣለች። ጡንቻዋ በመጠኑ ይወጠራል።
11. ድምጿ ያንተን ቅላፄ እንዲይዝ ትጥራለች። አንተ ድምዕህን ዝቅ አድርገህ የምታወራ ከሆነ እርሷም ድምጿን ዝቅ አድርጋ ማውራት ትጀምራለች።
12. በወሬአችሁ ጣልቃ ፀጉሯን ደግማ ደጋግማ ታስተካክላለች። ልክ የሆነ ሰው ለመሳብ እየተጣጣረች ያለች ያህል ራሷን ታስተካክላለች።
13. የእጇን መዳፍ ወዳንተ ታዞራለች።

ከእርሷ ምንም ምልክት ማየት ካልቻልክ ጊዜህን ማጥፋት የለብህም። አቀራረብህን አስተካክለህ እንደገና መሞከር አለብህ።

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ገና ከመጀመሪያው ልትቀርባት የማይገባህ ሴት የምታሳያቸው 6 ምልክቶች ተቀምጠዋል።

1. ለመጀመሪያ ጊዜ ስታገኛት መጠጥ እንድትገዛላት ከጠየቀችህ፤
2. በመጀመሪያ ቀጠሯችሁ ውድ ስጦታ እንድትወስድላት ከጠበቀች፤
3. ከመጀመሪያው ቀጠሮአችሁ በኋላ "ሲመችሽ ደውይልኝ" በላት። ከፈለገችህ ትደውልልህለች። ካልደወለችልህ እርሳት፤
4. ከሶስት ጊዜ በላይ ስራ እንደበዛባትና ለቀጠሮ እንደማይመቻት ከነገረችህ፤
5. ልትልክህ ወይም ጉዳይ እንድታስፈጽምላት ስትፈልግ ብቻ የምትደውልልህ ከሆነ፤
6. የወንድ ጓደኛ እንዳላት ካረጋገጥክ ወይም ከነገረችህ ወዲያውኑ አቋርጥ። በእርግጥ የምትፈልግህ ከሆነ ከእርሱ ጋር ያላትን ግንኙነት ሙሉ በሙሉ ማቋረጥ አለባት።

አንዲት ሴት የመቅረብ ሙከራህን ለሶስት ጊዜያት ያህል ካደናቀፈችብህ ምንም እንዳልተፈጠረ አስበህ ከጭንቅላትህ አውጣት። ምናልባት ልጅቷን በቀላሉ ልትተዋት ካልፈለግህና የመጨረሻውን አማራጭ መጠቀም ከፈለግህ በእድሜና በአካል የእርሷ እኩያ ከምትሆን ልጅ ጋር ተቃቅፈህ እየተሳሳቃችሁ በአጠገቧ እለፉ። ለአንተ ፍላጎት ካላት ስርቀህ ብታያት አትኩራ ስታያችሁ ታስተውላለህ። ይህን ካላደረገችና ምንም ሳይመስላት አልፋ ከሄደች አትፈልግህምና እርሳት።

## ምዕራፍ ሰባት

## ሴቶችን የትና እንዴት ማግኘት ይመረጣል

ለጊዜያዊ ጓደኝነትም ሆነ ለትዳር የምትመጥን ሴት ለማግኘት የሚረዱ የተለያዩ ዘዴዎች በተለያዩ ባለሙያዎች ሲጠቀሱ እናስተውላለን። እዚህ መጽሐፍ ውስጥ እየቀረበ ያለው ከሁሉም የላቀና እንከን የለሽ ነው ለማለት መቻኮል አያስፈልግም። ይሁንና በብዙ ሰዎች በተግባር ተፈትነው ውጤታማ የሆኑ ስለመሆናቸው ግን በእርግጠኝነት መናገር ይችላል። ሁሉም እንደ ግለሰባዊ እምነቱ እያጣጣመ ሊጠቀምባቸው የሚችሉ አማራጭ ክህሎቶች ተቀምጠዋል። እነዚህ ክህሎቶች ደግሞ ለወንደላጤ ወይም ለባለትዳር ተብለው የተፈረጁ አይደሉም። ወንደላጤ ሆኖ ከብዙ ሴቶች የምትስማማውን በመምረጥ ላይ የሚገኘውን፤ በጓደኝነት የተጣመራትን ሴት እንዴት አብራው እንድትዘልቅ ማድረግ እንደሚችል በመጠበብ ላይ ያለውን፤ ግራ ገብቶት ይህ ጨዋታ ይቅርብኝ ብሎ ከፍቅር ዓለም ራሱን ያገለለውን . . . ብቻ ለሁሉም ሊያገለግሉ የሚችሉ ክህሎቶች ናቸው።

### *ሴቶችን ለማግኘት የት መሄድ ይገባል?*

ሴት እንደምታስፈልግህ ከወሰንህ ሴቶች ወደሚገኙበት ቦታ መሄድ ግድ ይልሃል። ያኔ ያምትፈልጋትን ዓይነት ሴት የምታገኝበት አጋጣሚ ታገኛለህ። የምትፈልገው ቀጠን ሸንቀጥ ያለች ዓይነት ሴት ከሆነ ወደ ጅምናዝየም ዝለቅ ወይም ደግሞ ጅምናዝየም አካባቢ ወደሚገኝ ሱፐርማርኬት ወይም ጭማቂ ቤት ጎራ በል። የምትፈልጋት ሴት መንፈሳዊ ትሆንልህ ዘንድ ብትሻ ቤተክርስቲያናት አካባቢ ትኩረት አድርግ፤